# እ.ኤ.አ ሰኔ 16 ቀን የሚከበረውን ዓለም አቀፍ
# የቤተሰብ የሐዋላ ቀን

## *The International Day of Family Remittances (IDFR)*

## አስመልክቶ የተዘጋጀ ጋዜጣዊ መግለጫ

ሰኔ 2013 ዓ.ም

# እ.ኤ.አ ሰኔ 16 ቀን የሚከበረውን ዓለም አቀፍ የቤተሰብ የሬሚታንስ ቀን/The International Day of Family Remittances (IDFR) አስመልክቶ የተዘጋጀ ጋዜጣዊ መግለጫ

ዓለም አቀፍ የቤተሰብ የሐዋላ ቀን The International Day of Family Remittances (IDFR) በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባኤ የውሳኔ ቁጥር (A/RES/72/281) የፀደቀ እና በየአመቱ ሰኔ 16 ቀን የሚከበር ዓለም አቀፍ በዓል ሲሆን፣ ከ2015 ዓ.ም ጀምሮ በየአመቱ እየተከበረ ይገኛል፡፡ በዚህ ቀን በሀገር ውስጥ ያሉ ከ800 ሚሊዮን በላይ ቤተሰቦቻቸውን ሕይወት ለማሻሻል እና የልጆቻቸውን የወደፊት ተስፋ ብሩህ ለማድርግ እጅግ አስቸጋሪ በሚባል ሁኔታ ውስጥ ሳይቀር እያለፉ ወደሃገር ቤት ገንዘብ የሚልኩ ከ200 ሚሊዮን በላይ ስደተኞች አስተዋፅዖ ይዘከራል፡፡

በግለሰብ ደረጃ በሐዋላ መልክ የሚላከው ገንዘብ ሲጠራቀም የታዳጊ ሃገራት ዜጎች ህይወት ውስጥ እጅግ ወሳኝ የሆነ ለውጥ የሚያመጣ ነው፡፡ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ይህ በሐዋላ መልክ በታዳጊ ሃገሮች ላሉ ቤተሰቦች የሚላከው ገንዘብ ሀገራቱ ከዓለም አቀፍ ለጋሾች ከሚያገኙት ይፋዊ የልማት ዕርዳታ በሦስት እጥፍ ይበልጣል፡፡ ለምሳሌ ያህል በ2020 የፈረንጆች አመት ዝቅተኛና መካከለኛ ገቢ ያላቸው ሃገራት 540 ቢሊዮን ዶላር ከሐዋላ ማግኘት ችለዋል፡፡ ይህ ክንውን የኮቪድ ወረርሽኝ ባሳደረው ተጽዕኖ ምክንያት ከቀዳሚው 2019 ዓ.ም በ8 ቢሊዮን ዶላር ያነሰ ነው፡፡

ይህን ሃቅ በመረዳትም በተባበሩት መንግስታት ዘላቂ የልማት ግቦች ትግበራ ላይ በሐዋላ መልክ ለአለማችን ደሃ ሃገሮች የሚላከው ገንዘብ ትልቅ ስፍራ ተሰጥቶታል፡፡ ትንበያዎች እንደሚያሳዩት ከ2015 እስከ 2030 ባለው የዘላቂ ግቦች ትግበራ ወቀት አንድ ቢሎዮን ሰዎች በላኪነትና ተቀባይነት የሚሳተፉ ሲሆን፣ 8.5 ትሪሊዮን የአሜሪካ ዶላር ወደ ታዳጊ አገሮች እንደሚላክ ይጠበቃል፡፡ ይህ ገንዘብ በአብዛኛው የሚላከው በድህነትና ርሃብ የተጎዱ የገጠር አካባባዎች በመሆኑ ጠቀሜታው እጅግ የጎላ ነው፡፡ እነዚህ የገንዘብ ድጋፎች በታዳጊ ሃገራት የሚገኙ ተቀባዮች የተባበሩት መንግስትታ ዘላቂ የልማት ግብ አጀንዳዎችን ማለትም ድህነት ቅንሳ፣ የተሻለ የጤና አጠባበቅ እና የተመጣጠነ ምግብ ሽፋን ማደግ፣ የትምህርት ዕድሎች መስፋፋት ፣ የተሻሻሉ መኖሪያ ቤቶች እና የአካባቢ ጽዳትና ንፅህና፣ ሥራ ፈጠራ፣ የፋይናንስ አገልግሎት ተደራሽነት፣ ፍትሃዊ ተጠቃሚነት እና ሌሎች የልማት ግቦቹ መገለጫዎችን በቤተሰብ ደረጃ እዲያረጋግጡ የሚያግዝ ነው፡፡

ኢትዮጵያ በርካታ ዜጎቻቸው ለሥራ ፍለጋ፣ ለኑሮና ለትምህርት በተለያዩ የዓለም ክፍሎች ከተሰደዱባቸው ሀገራት መካከል ትመደባለች፡፡ እነዚህ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ሀገርቤት ለሚኖሩ ወደጅ ዘመድ ኑሮ መደጎሚያ፣ ለቤትና ሌሎች ቋሚ ንብረቶች ግንባታ በተወሰነ ደረጃም ለኢንቨስትመነት የሚሆን የውጪ ምንዛሬ ይልካሉ፡፡ ይሁንና ካለው እምቅ ሀብት አንፃር

በሐዋላና  ኢንቨስትመንት መልክ ወደሀገር ውስጥ የሚገባው የውጪ ምንዛሬ እጅግ ዝቅተኛ የሚባል ነው፡፡ በተለይ በአፍሪካ ውስጥ ይህን ሃብት በአግባቡ ከተጠቀሙበት እንደ ናይጄሪያ፣ ኬኒያ፣ ጋና የመሳሰሉ ሃገራት ክንውን ጋር ሲነፃፀር ዝቅተኛ የሚባል እንደሆነ ይጠቀሳል፡፡ እነዚህ በርካታ ኢትዮጵያውያን ለወዳጅ ዘመዶቻቸው ወደሃገር ቤት ከሚልኩት ገንዘብ ውስጥም የተወሰነው ወደጥቁር ገበያ የሚገባ በመሆኑ ሀገራችን የሚያስፈልጋትን የውጪ ምንዛሬ በተፈለገው ጊዜና ሰዓት እንዳታገኝና የተገኘው ገንዘብም ለታለመለት ዓላማ እንዳይውል እያደረገ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ላለፉት በርካታ አመታት በውጪ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ጥረት ለመደገፍ ዘርፍ ብዙ ተግባራትን እያከነወነ ይገኛል፡፡ ወደሃገራችን ከሚገባው የውጪ ሃገር ገነዘብ ገቢ አብዛኛው የሚሰበሰበው በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በኩል ነው፡፡ በያዝነው የ2013 የበጀት አመት እስከ ግንቦት 30 ባለው  የ11 ወር ጊዜ ውስጥ ምንም እንኳ የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ተጽዕኖ ቢኖርም 2.4 ቢሊዮን ዶላር የሚጠጋ ገንዘብ በባንካችን በኩል ወደሃገር ውስጥ ገብቷል፡፡

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ትላልቅ ሃገራዊ ፕሮጀክቶችን በገንዘብ ከመደገፍ አንፃር እንዲሁም በህብረተሰቡ የዕለት ተዕለት ኑሮ አስፈላጊ የሆኑ መሰረታዊ ሸቀጣ ሸቀጦች ወደሃገር ውስጥ ለማስገባት የሚያስፈልግ የውጪ ምንዛሬ ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡ ይህን ኃላፊነቱን ለመወጣት ሐዋላ ጨምሮ ሌሎች የውጪ ምንዛሬ ምንጮችን ለማሳደግና ያለውን አምቅ ሃብት አንጠፍጥፎ ለመጠቀም የሚስችሉ በርካታ ጥረቶች ይደረጋሉ፡፡

የሐዋላ ገቢያችንን ለማሳደግ ህጋዊውን የባንክ አሰራር መከተል እጅግ ወሳኝ ቢሆንም ባለፉት አመታት ይህን እምቅ ሃብት በአግባቡ ከመጠቀም አንፃር የጥቁር ገበያ መስፋፋት ለዕቅዶች አለመሳካት ዋነኛ ምክንያት ሆኗል፡፡ ባለፈው አመት ተከስቶ የአለማችን ዋነኛ የኢኮኖሚ ችግር ወደመሆን የደረሰው የኮቪድ-19 ወረርሽኝም ባለፉት ሁለት አመታት ለተስተዋለው የረሚታንስ ገቢ መቀነስ ትልቅ አስተዋጽኦ ነበረው፡፡

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከሐዋላ የሚገኘው ገቢ ለሀገር ኢኮኖሚ ያለውን ግዙፍ ፋይዳ በአግባቡ ይገነዘባል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የደንበኞቹን የውጪ ምንዛሬ ፍላጎት ከማርካት አንፃር የረሚታንስ ዕድሎችን ማስፋት እጅግ አስፈላጊ መሆኑንም ይረዳል፡፡ በዚህ ምክንያትም የውጪ ምንዛሬ ግኝትን ማስፋት በባንካችን ስትራቴጂ ውስጥ ዋና ጉዳይ ሆኖ ተይዟል፡፡ ይህን ተግባራዊ ለማድግ ከሚደረጉ ጥረቶች መካከልም፡-

- በውጪ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ወደሃገር ቤት የሚልኩትን የውጪ ምንዛሬ ለማሳደግ የሚረዱ የፕሮሞሽን ስራዎች እየከናወነ ይገኛል፡፡ በዚህ ረገድ ልዩ ልዩ

የምክክር መድረኮችን ማዘጋጀትና በሌሎች ለተዘጋጁ መድረኮች ድጋፍ ማድረግ ተጠቃሽ ክንውኖች ናቸው፡፡

- ለላኪዎችና ተቀባዮች የተመቹ፣ ቀላልና ከአደጋ የጸዱ በቴክኖሎጂ የተደገፉ አሰራሮችን ተግባራዊ ለማድረግ ጥረት ይደረጋል፡፡ ይህን አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል የቴክኖሎጂ ግዢ ተፈጽሟል፡፡
- በውጪ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በሀገራቸው ቤት ለመስራትና ሌሎች ቋሚ ንብረቶችን ለማፍራት የሚያስችላቸው ብድር በማመቻቸት በርካታ የውጪ ምንዛሬ ወደሃገር ውስጥ እንዲገባ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡
- "ይቀበሉ፣ ይመንዝሩ፣ ይሸለሙ" የተሰኘ የሽልማት መርሐ-ግብር በማዘጋጀት ዜጎች ከውጪ የሚላክላቸውን ገንዘብ ከባንክ ብቻ እንዲቀበሉ የማበረታታት ሥራ በሰፊው እየተሰራበት ይገኛል፡፡ በ21 ዙሮች ለተካሄዱ መርሃ-ግብሮች ከ46.2 ሚሊዮን ብር በላይ ግምት ያላቸው ሽልማቶችን ለደንበኞች በመሸለም ትልቅ የፕሮሞሽን ስራ ተከናውኗል፡፡
- የጥቁር ገበያውን ተጽዕኖ ለመቀነስ በሚደረገው ሀገር አቀፍ ጥረት ውስጥ የመፍትሄው አካል ለመሆን እየተሰራ ይገኛል፡፡

በዓለም አቀፍ ደረጃ ጁን 16/ሰኔ 9 ቀን የሚከበረውን ዓለም አቀፍ የሐዋላ ቀንን ባንካችን በተለየ ሁኔታ እንዲከበር ወስኗል፡፡ ቀኑ እንዲዘከር ያስፈለገበት ዋነኛው ምክንያት በሀገር ልማት ውስጥ ወሳኝ ቦታ ያለው የውጪ ሃገር ገንዘብ ግኝታችን በመደበኛው የባንክ ሥርዓት ውስጥ እንዲያልፍ መልዕክት የማስተላለፊያ መድረክ መፍጠር ነው፡፡ ህብረተሰባችንን የማንቃት ተግባር በአግባቡ ከተከናወነ በርካታ ታዳጊ ሃገራት በዘርፉ ከደረሱበት የተጠቃሚነት ደረጃ መድረስ እንደሚቻል የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በጽኑ ያምናል፡፡